የረቡዕ ሚያዚያ 5 1997 ዓ.ም ( ኤፕሪል 13 2005 )

## የፍኖተ ዴሞክራሲ ሐተታ

## የሕዝቡ ትግል ፍሬ እንደገና እንዳይነጠቅ

ጮሌዎች ከየዋሆቹ በራፍ ሞፈር ይቆርጣሉ እንደሚባለው፥ ሠላማዊው ሰው ሳያውቅ፥ ሳይጠነቀቅ፥ ይህ ይሆናል ብሎ ሳይጠረጥር፥ ሳይዘጋጅ፥ ሳይደራጅ እየቀረ፥ ሁሌ መብት-ነፃነቱን፥ ሐብት-ንብረቱን፥ ሰብዓዊ ክብሩን፥ ደስታና ሀሴቱን፥ በዘራፊዎች፥ ሲነጠቅ ኖሯል፡፡ ይህ ክስተት በታሪክ ሂደት ውስጥ የነበረ ነው፡፡ ማነኛውም ሕዝብ ይህ ዝርፊያና ንጥቂያ የሚካሄድበት፥ በተደራጀ ኃይልና ቡድን ብቻ ሳይሆን፥ ወይም ደግሞ የመንግሥት ሥልጣን ለመጨበጥ ባቀበቀቡና አድፍጠው በሚጠባበቁ ከፍሎች ብቻ ሳይሆን፥ እንደ ዕንግዳ ደራሽ፥ እንደ ውሃ ፈሳሽ በሆኑና በውጭ ኃይል በተዘጋጁ ፈጥኖ ደራሽ ኃይሎችም ጭምር ነው፡፡ እነኝህ ተጠቃሽ ክፍሎች አንድ የሚያርጋቸው ባኅርይና ተግባር አላቸው፡፡ ሁሉም የሕዝቡን ብሶትና እሮሮ በውሸትና በማጭበርበር ማስተጋባታቸው ነው፡፡ ሀዘንህ ሀዘናችን፤ ጭቆናህ ጭቆናችን፥ በደልህ በደላችን፤የልብህ ትርታ በጆሮአችን እያሉ የአዞ እንባ በመርጨት በኩል ተመሳሳይ ክፉና ግብዝ ሰብዕና አላቸው፡፡ የተደበቀ ውጥናቸው/አጀንዳና ዓላማቸውን፥ ከሕዝብ ትግል ጎን ቆመናል በሚል ለምድ ሸፍነው ይቆያሉ፡፡ ሕዝቡ ከጨቋኝ ገዥዎቹ ጋር በሚያደርገው ግብግብም፥ አለንልህ፥ ያዘው፥ ልቀቀው እያሉ ይቆዩና፥ ልክ አምባገነኑ ሥርዓት በሕዝቦች መራራ ትግልና መሥዋዕት ሲገረሰስ፥ ወዲያውኑ፥ የሕዝቡን ትግል ነጥቀው ወደ ሥልጣን ኮርቻ ለመውጣት ይራኩታሉ፡፡ የመንግሥት ሥልጣን ይጨብጣሉ፡፡ በሚያስገርም ፍጥነትም፥ አለንልህ ሲሉት የነበረውን ሕዝብ ፥ ይክዱታል፥ ያገልሉታል፥ ይጠሉታል፥ ይጠረጥሩታል፥ ይፈሩታል፥ ብሎም በአዲስ መልክ ወደ ተዘጋጀ አዲስ ዕልመተ- ሥርዓት ያስገቡታል፡፡ አዲስ አስቸኳይ ዐዋጅ ያውጃሉ፡፡ የሰዓት እላፊ ገደብ ያበጁበታል፡፡ በዓዲስ ዓይነትና ዘዴ ወደ ተዘጋጀ የጭቆና አገዛዝ እንዲሸጋገር በስነልቦና ያዘጋጁታል፡፡ሳይፈልጋቸው ሞግዚትህ ነን ብለው ይሰየሙበታል፡፡ ለዚህ ሁሉ ድርጊታቸው የሚጠቀሙበት ማጠየቂያ፥ ያው የተለመደውን፥ ያረጀ ያፈጀውን አሳፋሪ ፕሮፓጋንዳ ይሆናል፡፡ ይኸውም፥ ሕዝቡ፤ አልነቃም፥ አልተደራጀም፥ አልተዘጋጀም፥ የራሱን መሪዎች ለመምረጥ ጊዜው አሁን አይደለም የሚል ነው፡፡ በዚህ መልክ ሀገሪቱን ለማጥፋት፥ ሕዝቡንም በአዲስ የብረት መዳፍ ለመጨቆን የሚያስችላቸውን መሠረት ይጥላሉ፡፡ ይትገሉን ፍሬ እንዳይነጠቅ መብቱን ዛሬ ለጊዜው ማገድ የግድ ነው፤እኛም ጊዜያዊ ነን ብለውም ይጮኻሉ፡፡ እበላ ባዮችን አሰልፈውም አዎን ልክ ነውን ያስለፍፋሉ፡፡ ከዚያ ወዲያማ የሚፈፀመውን ሂደት መዘርዘር አስፈላጊ መስሎ አላገኘነውም፡፡ ሕዝቡ የሚያውቀውና ፍዳውን ሲቆጥር የነረበት ክስተት በመሆኑ ነው፡፡

የሕዝቡ የትግል ድል፥ በአልተጠበቀ ሁኔታ፥በአዲስ አምባገነኖች በመነጠቁ፥ ሀገሪቱና ዜጎቿ ወደ ሌላ የመከራ አዙሪት ይገባሉ። አሮጌው መከራና ፍዳ፥ በአዲስ የጭቆና አገዛዝ ሰቆቃ ይተካል። የፊተኛውን በማስጠላት አዲሱን በማሞገስ ረገድ የሕዝቡን ሥነአዕምሮ ለማደንዘዝ ይህ ነው የማይባል፥ ያልተቋረጠና አደንዛዥ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ያካሂዳሉ። ሕዝቡ እንዳይደራጅ፥ ሌሎቹም የኅብረተሰብ ክፍሎች በነፃ እንዳይፈጠሩ፥ አዳዲስ አማቂ ህጎች ይወጣሉ። መከረኛው ሕዝብም፥ ትሻለን ስድጀ ትብስን አመጣሁ ከማለት ሌላ የሚተነፍስበት ሁኔታ አይኖረውም። ዉሃ ቀድቶ ውሃ መመለስ፥ በቆየ ችግር መላወስ፥ በነበረ የኑሮ ፍዳ መርመርመስ፥ የአዲስ ተስፋና ራዕይ መጨለም፥ ዙሪያው ገደል የሆነ ኑሮን መግፋት፥ ከሙታን በላይ ከህያው በታች መጠራሞት፥ በገዥዎቹ ላይ ብቻ ሳይሆን፥ በራስም ላይ ቢሆን ዕምነት ማጣት፥ የአትዮጵያ ሕዝብ ዕጣ ፈንታ ተደርጎ እየተወሰደ መምጣት፥ እጅግ ተስፋ አስቆራጭ መሆኑ፥ ማንም ዜጋ የማይረዳው ክስተት አይደለም።

ሲሾም በልቶ ያላበላ፥ ራሱን ጠቅሞ፥ ዘመድ ወዳጁን ያልጠቀመ ፥ እርጉም እንደ አርዮስ የተባለ ይመስል፥ አንድ ጊዜ ሥልጣን ላይ ከወጡ፥ ታገልንለት የሚሉትን ምልዐተ ሕዝብ እየዘረፉ ዘመድ ወገናቸውን ይጠቅማሉ ፥ ያበለፅጋሉ። ሕዝብ እየዘረፉ ራስን ማበልፀግ ደግሞ፥ በሦስተኛው ዓለም ተብሎ በሚጠራውና በተለይም በአፍሪካ ክፍለ ዓለም ፀያፍ ቢሆንም የተለመደ በመሆኑ፥ በሙስና መዘፈቅ አያስጨንቃቸውም። የኅሊና ፍርድም ይሁን የታሪክ ወቀሳ አይከነክናቸውም። አምባገነኖች የሚያወጡት ሕግና የሚደነግጉት ደንብ እነርሱን ስለማይመለከታቸው፥ የህግ ተጠያቂነት፥ አይታያቸውም። ለሕዝብ ፍራቻ፥ ግድ የላቸውም። ይህ ዕውነታ በሦስቱም ተፈራራቂ አምባገነን ገዥዎች የነበረና ያለ ነው። ወደ ፊትም መልኩን እየለዋወጠ እንዳይቀጥል ለማድረግ ዋስትናም ይሁን መከላከያ ለማግኘት የሚቻላው ግን፥ በአንድ መሠረታዊ ጉዳይ ላይ ሕዝቡ ዕርግጠኛ ሲሆን ብቻ ነው ብለን እናምናለን። ይኸውም፥ ታግሎ ያገኘውን ድል ቀማኞች እንዳይነጥቁት ነቅቶ መጠበቅና ከእጁ እንዳይፈለቅቁት መከላከል ብቻ ነው። ይህን ለማድረግ ደግሞ፥ በነፃ መደራጀትና የራሱን መሪዎች ማዘጋጀት ወሳኝነት አለው። ሕዝቡ ተደራጅቶ የሚያምናቸውን መሪዎቹን በመምረጥ፥ ትግሉን በአስተማማኝ ሁኔታ መቆጣጠር፥ ድሉን በጭልፊቶች እንዳይነጠቅ ዋስትና ያገኛል። በትግሉ ሂደት ፥ ማነኛውም ዜጋ በነፃ ተደራጅቶ መታገል ማለት፥ አምባገነኖቹ ሲንገዳገዱ፥ የሕዝቡን ድል በመንጠቅ ህጋዊ ባልሆነ መንገድ፥ ሥልጣን ለመውሰድ የሚያቆበቁብትን ነጣቂዎች ለመከላከል ያስችለዋል። እዚህ ላይ፥ አጽንኦት ሊሰጥባቸው የሚችሉ መሠረታዊ ጉዳዮች መኖራቸውን፥ ማስገንዘብ እንሻለን። እነርሱም:-

- አምባገነኖችን ለመጣል በሚደረገው ሀገራዊ ትግል ሂደት፥ ሁሉም ዜጋ በሚያምናቸው ድርጅቶች ውስጥ እየገባ ተሳትፎ ሊያደርግ ይገባል።
- የተቃዋሚ ድርጅቶችም፥ ሕዝቡን የማደራጀትና በትግሉም ንቁ ተሳትፎና ትብብር እንዲያደርግ ሁኔታዎቹን ሊያመቻቹለት ይገባል።

- ምልዐተ ሕዝብን ያላቀፈ ትግል ሁሉ ምንጊዜም ቢሆን፥ ለማንኛው አደጋ የሚጋለጥ መሆኑን መገንዘብ ማለት፥ አሮጌ አምባገነን ሲገረሰስ፥ ሌላ አዲስ አምባገነን እንዳይተካ ይረዳል ማለት ይሆናል፡፡ የትግሉ ሜዳ አገዛዙ በሚለው መስክ ሳይሆን ሕዝብ ሆ ብሎ በሚነሳበት የአመፁ መንገድ መሆንም አለበት፡፡
- ይህም በበኩሉ፥ ሀገራችን ለአለፉት ሠላሳ ዓመታት ከተጠናወታት የመከራና የጭቆና አዙሪት እንድትላቀቅ ይረዳታል ማለት ነው፡፡
- ከሁሉ በላይ ግን የዴሞክራሲ ሥርዓትን መሠረት ለመጣል፥ የተመቻቹ ሁኔታዎች ሊፈጠሩ የሚችሉበት ዕድል ሰፊ ይሆናል ማለት ነው፡፡

እነኝህ ሁሉ መሠረታዊ ጉዳዮች ባልተሟሉበት ሁኔታ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ መራራ ትግል የተጠበቀውን ውጤት ሳያገኝ፥ ግቡንም ሳይመታ፥ በአዳዲስ አምባገነኖች መነጠቁ ሊያስደንቅ አይችልም፡፡ ሌላው ቢቀር ታዲያ ፥ የተቃዋሚ ድርጅቶች፥ ለራሳቸው ኀልውና እንኳ ብቻ ሲሉ፣ ተባብረው፥ ሕዝቡን አስተባብረው ቢታገሉና ያለውን አምባገነን ሥርዓት አስወግደው፥ ሌላም አምባገነን እንዳይከሰት ለማድረግ መጣር ቢችሉ፥ ምንኛ ሀገሪቱ በታደለች ብሎ ሕዝቡ ቢመኝ፥ የህልም እንጀራ እንደ መብላት ሊቆጠርበት አይገባም፡፡

ሕዝቡ ባላሰበው፥ ባልተመኘውና ባልታገለበት ሁኔታ፥ የየካቲቱን ሕዝባዊ ድል በጥቂት ጮሌ የጦር መኮንኖችና ተባባሪዎቻቸው ተነጠቀ፡፡ ይህ አልበቃ በሎ፥ ከአስራ ሰባት ዓመታት መራራ ትግል በኋላ ደግሞ አገዛዙ ሊወግድ ሲል፣ በባዕዳን በተደገፈ የብሔር ድርጅት የተመኘውን ነገውን ተነጠቀ ፡፡ በኀሳ ላይ የተመሠረተ አምባገነን ሥርዓት አምጥቶ፥ ይኸው ወሮበላው ቡድን ሀገሪቱን እያመሳት ይገኛል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ አይለፍልህ፥ ከመከራም አትውጣ ተብሎ የተረገመ ይመስል፣ ዕጣ ፈንታው በጦርነትና በብጥብጥ፥ በስደትና በዕስራት፥ ነፃነት በማጣትና በፍትኅ ርትዕ መጓደል አዙሪት ውስጥ ገብቶ የመከራ ኑሮውን ይገፋል፡፡ ከዚህ አዙሪት መውጣት መቻል አለብን፡፡ በውድም ይሁን በግድ!

ከዚህ አዙሪት ግን በቀላሉ መውጣት የሚቻል አይሆንም ፡፡ ብዙ ታላላቅ ተግባሮች መከናወን አለባቸው፡፡ ከላይ በአጭሩ የተጠቀሱት መሠረታዊና ወሳኝ ጉዳዮች እንዳሉ ሆነው፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ የትግል ድሉን እንዳይነጠቅና ብሎም፥ ለሌላ አዲስ አምባገነን ሥርዓት እንዳይዳረግ ከሚያስችሉት መከላከያ ዘዴዎች አንዱ፥ ለሽግግር ወቅት የሚሆን ስልትና ዕቅድ/ስትራተጂ መንደፍና በተግባር ለመተርጎም መዘጋጀት ይመስለናል፡፡ ምን ጊዜም ቢሆን አምባገነን ሥርዓት በሕዝብ ኃይል መገርሰሱ የማይቀር ነው፡፡ የማነኛውም የፖለቲካ ትግል የመጨረሻ ግብ ግን አምባገነን ሥርዓትን መገርሰስ ብቻ ሊሆን አይችልም/አይገባውምም፡፡ የመጨረሻ ግቡ፥ የዲሞክራሲ ሥርዓትን መመሥረትና ሕዝቡ የሥልጣን ባለቤት የሚሆንበትን ሂደትና አፈፃፀም ማመቻቸት ይሆናል፡፡ ይህ ከባድ ሀገራዊ

ተልዕኮ ደግሞ፥ በጥቂት የሥልጣን ጥመኞች፣ ወይም፥ ቡድኖች የሚከሰት አይሆንም። ሁሉንም የሀገሪቱን ዜጎች በሚያሳትፍ መድረክና ሥርዓት ብቻ ነው ሊሳካ የሚችለው። አስተማማኝ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመመስረት በግድ ሁሉንም የሚያሳትፍ፣ ማለት፥ አሳታፊ ዲሞክራሲ በተግባር ሊተረጎም የሚያስችል ሰፊ መድረክ ሊኖር ይገባል። አብሶማ እንደ ኢትዮጵያ በብዙ ብሔር-ብሔረ ሰቦች በታደለች/ በበለፀገች ሀገር፥ አስፈላጊነቱ/አስገዳጅነቱ ለውይይት የሚቀርብ አይሆንም። ከእንግዲህ ወዲህ፥ በኢትዮጵያ የፖሊቲካ መልከዐ-ምድር ሊሆን/ሊመሰረት የሚገባው፥ ሁሉንም ዜጎች ያካተተ ሥርዓት ብቻ ነው። ዘላቂ ሠላምና መረጋጋት፥ ዕድገትና ብልፅግና ሊገኝ የሚችለውም ይህ የፖለቲካ ሥርዓት ሲሰፍን ነው ብሎ ማመንና ይህም ዕውን እንዲሆን መታገል፥ ሌላ አማራጭ አይኖረውም። የሕዝብን ድል በጮሌነት እየነጠቁ የአምባገነን ሥርዓት መመስረት የትም እንዳላደረስን፥ ለእኛ ኢትዮጵያውያን ሊነግረን የሚችል ባዕድ የለም። እኛ እናውቅልሀለን ልንባልም አይገባም። ለአያሌ ዘመናት የራሷን መንግሥት መሥርታ የቆየች ሀገር፥ ምን ዓይነት የፖለቲካ ሥርዓት መኖር እንዳለባት፥ ባዕዳንም ይሁኑ ቅጥረኞቻቸው ሊወስኑላት አይችሉም። እኛም ልንፈቅድላቸው አይገባንም። ብልኀ ሳንሆን ቀርተን ጮሌዎቹ የትግላችንን ድል እንዳይነጥቁን ነቅተን መጠበቅ ብቻ ሳይሆን፥ የትግላችንን ድል ፍሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ተጠቃሚ እንዲሆን ተባብረን ከመታገል ሌላ አማራጭ አይኖረንም። ይህ ሳይሆን ቀርቶ፣ አሁንም እንደ ትላንቱ፥ የሕዝቡን ድል፥ አድፍጠው ለሚጠብቁ ነጣቂዎች ካስወሰድን፣ በኃላፊነት የምንጠየቀው እኛው ራሳችንን እንጅ፥ ሌላ ሊሆን አይችልም። ዘለዓለም በባዕዳንና በሀገር ውስጥ ቅጥረኞቻቸው ብቻ እያማካኘን መኖር ኢትዮጵያዊ ባኅርይ አይደለምናም ነው።

ስለዚህም በትግል መብታችንን ለማስከበርና ሀገር አጥፊውን አገዛዝ ለማስወገድ፣ብሎም ሕዝባዊ ድልን ለማስከበር በጋራ ለወሳኙና ለመጨረሻው ትግል እንነሳ የሚለው ጥሪ እያስተጋባ ነውና ጆሮ እንስጠው። እንድ መና ከሰማይ ዱብ የሚል ወይም በመለስዘ ስናዊ መልካም ፈቃድ የሚገኝ ዴሞክራሲ ሆነ መብት የለም። ወደፊትም ከቶ የሚኖር አይደለም። ሀገርን ለማዳን ሆነ መብትን ለማስከበር በቅድሚያ ያለውን ጋሬጣ ማለትም የመለስን ቡድን ከሥልጣን ማስወገድ የግድ ያስፈልጋል። ይህን አሌ የሚሉ ካሉ ሰልፋቸው ከሕዝብ ጎራ አይደለምና ለአወናባጆችና ለድል ነጣቂ/አስነጣቂዎች ተሸናፊ አንሁን።